# እድሜ ዘልዛላው! ወይስ ካረጁ አይበጁ? ለኢንጂነር ኃይሉ ሻውል

**ጉልላት ኃይሉ**
**ከሴንት ሊዊስ/ አሜሪካ።**

መቸም የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ በምምጣቱ፤ ስሜትን ተቆጣትሮ ከየት ላይ ጅምሮ፤ የት ላይ እንደሚቋጭ ግራ አጋቢ ቢሆንም፤ "ያለውን የወረወረ ፈሪ አይባልም" እንዲሉ፤ እስኪ እኔም ሰሞኑን እንደ ሸማ መስሪያ መወርወሪያ እዚያው! እዚያው! የሚወረወረውን የሰሞኑን የአገራችን ፖለቲካ በተመለከተ ትንሽ እንድል ይፈቀድልኝ።

ባለፈው ወር መጨረሻ፤ ማለትም፤ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ጥቅምት 30/ 2009 ዓ. ም. በቆራጡ አገር ወዳድና አምበሳው የመዓድ መሪያችንና፤ በሁለት ማንዴላዎቻችን አፋጠና አስጨንቆ ኢሃዴግን ከሁለት ወር ድርድር በኋላ በሻራተን ሆቴል የተደረገውን የነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ማሰሪያ ውል የተፈራርሙባትን ቀን እንደ የአድዋ ድል በዓል ለማክበር በዘመን መቁጠሪያ ሰሌዳችሁ ላይ ሳታጠቁሩ እንዳልቀራችሁ አልጠራጠርም:፡

በጣም የምወዳቸው፤ ነገር አዋቂ፤ ነገሮችን ሁሉ ከምሳሌ ጋር እያጣጣሙ ይናግሩ የነበሩ የሴት አያቴ፤ አንዳንድ በጣም ያልጠበቁትና ያልታሰበ ነገር ሲያጋጥማቸው፤ አገጫቸውን በመዳፋቸው ደገፍ አድርገው፤ አምስት ጣቶቻቸውን ጉንጨቻቸው ላይ ለጥፈው፤ "አይ እድሜ ዘልዛላው"! ሲሉ፤ በነበረኝ ነገርን የማጣጣም አቅምና ለጋ አይምሮዬ እንዲሁ የአንዷ አያቴ መውነኛ (መረግረጊያ) አድርጌ እመለከተው ነበር። ለካስ በመኖር ብዛት የነበረው እንዳልነበር፤ ያልጠበቁት ሳይታሰብ እንደ መርዶ በጥዋት ሲደመጥ፤ እንዲህ ከባድ ነገር በመሆኑ፤ ከአምላክ የተሰፈረን እድሜ እስከ ማማረር የሚያደርስ የስሜት መግለጫ ኖሯል።

አንዳንዴ እኔም ወደ መጨረሻው አርባዎቹ በመሆኔ፤ እድሜ ዘልዛላው የሚያሳየኝንም ይሁን፤ ሳረጅ እንደማልበጅ በመፍራት፤ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ በነብያት አፍ ሲመሰከር ይሰማና  ምጣቱንም ይጓጓ የነበረው የእድሜ ባለፀጋው ሰሞኦን፤ በመጨረሻዋ ዬእድሜው ማገባደጃ ጌታ በበረት እንደተወለደ ምኞቱ ይሞላለት ዘንድ፤ እግዚአብሔር አምላክ ከማንም ቀድሞ ጌታን እንዲታቀፍ እድሉን እንደሰጠው፤ እሱም ይህን ፀጋ በማግኘቱ፤ "አምላክ ሆይ አንተን ባየሁበት አይኔ ሌላ መጥፎ ነገር ሳላይ ዬእድሜየ ፍጻሜ አድርግልኝ" ብሎ አማላኩን ተማጸነው ሁሉ፤ እኔም ምንም በእድሜ ዘመኔ ሁሉ ጥሩ ነገር ባላይም፤ ከከፋው የአገርና የሕዝብ በደል በላይ የከፋውን

ዬእንጂነር ኃይሉን ክህደት ፈጻሚ ሳላይ የዚህ ዓለም ጣጣ እንዲያበቃልኝ ከምመኝበት ወቅት ላይ ደርሻለሁ። እናንተስ ወገኖቸ ምን ትመኙ ይሆን?

እርገጠኛ ነኝ፤ ከአርባዎቹ እድሜ ክልል በላይ ያላችሁ፤ በታሪክ የነ አጼ ቴዎድሮስን፤ የነ ኣጼ ምኒሊክን ያነበባችሁና የምታደንቁ። በተግባር ደግሞ "እምቢ ለነፃነቴ፤ እምቢ ለፋሽስቶች፤ ሥጋየን እንጅ ነብሴን ጠላት አይጫወትባትም" ብለው፤ የዓላማቸውን ጽናት፤ እንዲሁም የአገርና ሕዝባዊ ፍቅራቸውን ብርታት፤ ትውልድ ሁሉ ይከተለው ዘንድ በፎቅ ተወርውረው መስዋእት የሆኑትን፤ የዚያ የሥድሳ ስድስቱ ትውልድ ቀራጥ መሪ ተሥፋዬ ደበሳይንና የሱ ፋና ወጊ በመሆን በከተማና በገጠሩ ከፋሽስቱ ደርግ ጋር የተዋደቁትን። በኋላም ከጎጠኛው ወያኔ ጋር ሲፋለሙ ያለፉትን እነ ጋይም ገ/እግዚአብሔርን የምታውቁ ሁሉ፤ እንደ አያቴ እድሜ ዘለዛላ ሆኖ ብዙ ጨጓራ ላጨች፤ በአገርና በህዝብ ሥም እየማሉ፤ የራሳቸውን ህሊና የሸጠ ዘመናዊ ኑሯቸውን ሲያቀማጥሉ ኑረው ዛሬም ዓለሙን ሊሰናበቱ ቅዳሜ ላይ ሲደርሱ ታሪካቸው ከነ ሆድ አምላኩ ስንክሳር እንዳይወጣ የመጨረሻ ቁርባናቸውን ከወያኔ ቤተ-መርከስ ሲቀምሱ ማየታችን ሁላችንም በአንድ የቁጭት ሰረገላ እንደሚያከንፈን አልጠራጠርም።

ልብ እንበል! ዛሬ የምንኮራባትን ኢትዮጵያችን እንደኩታ ገጣጥመው ታሪክ የሰሩት አጼ ቴዎድሮስ፤ እንደ እሳቸው የአገርና የወገን ፍቅር ያላቸው በብዙ መቶ ሺ ተከታይ የነበራቸው ቢሆንም፤ ስልጣኔን ይቀናቀናል ብለው ያሰቡትንና በነፍጥ ተይዞ በተመሰከረበት ላይ ይውሰዱ በነበረው እጅግ ርህራሄ የጎደለው እርምጃ ብዛት ተማሮ የነበረው ህዝባችን፤ ጊዜና ሁኔታን ጠብቆ ቁጭቱን እንዴት እንደሚበቀል ሲያስብና ሲያንሰላስል ቆይቶ፤ አጋጣሚው ሲያመቸው ቂሙን በሆዱ አርግዞ እያቅራራና እየፎከረ መቅደላ ድረስ አብሮአቸው ዘምቶ "የጠላቴ ጠላት፤ ወዳጅ ነው" በሚል የሞኝነት ፈሊጥ ለጉድ ጎልቷቸው በመሸሸ ተበቀላቸው። እሳቸውም፤ ጠላትን በብቸኝነት መጋፍጥ እንደማይችሉ አይተው ራሳቸውን እንዲሰው መገደዳቸውን ታሪክ ያስነብበናል።

የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ደግሞ፤ በምርጫ 97 እውነትም የለውጥ ሃዋሪያ ናቸው በሚል፤ ማንዴላ! ማንዴላ! እያለ በራሱ ላይ ተሸክሞ የጨፈረው ህዝባችን፤ ዛሬ ስማቸው በጋዜጣ፤ ሥዕላቸው በቴሌቭዥን መስኮት ብልጪ ሲል በሙሉ ዓይኑ ሊያያቸው እንደማይፈልግ ማየታችን፤ ገና ንፋስ ያልመታው ሃቃችን ነው።

አምባገነኖች ልብ ያላሉት ነገር ግን ቢኖር፤ ገናናነታቸው በአንድ ወቅት አለሁ! አለሁ! በሚል የተሸፈነውን ውጪያዊ ቅባቸውን ብቻ በማየት፤ ውስጣቸውን ሳይመረምር፤ እውነትም ፍቅሩ ከውስጥ የፈለቀ፤ አገራዊና ህዝባዊ ሃላፊነትን የሚሸክምልኝ መሪ መጣ ብሎ በፍቅር አጅቧቸው ከሚወጣ የህ/ሰብ ክፍል የሚሰጥ የክብር ፀጋ መሆኑን ዘንግተው፤ ከሰማዩ ሰማየት የወረደላቸው፤ አስቀድመው እንደ ሙሴ ኢትዮጵያን እና ሕዝቧን ሊታደጉ የተዘጋጁና የተመረጡ አስመስለው በወገናቸው ላይ ሲሰለጥኑ፤ በአንጻሩ ደግሞ የሰቀላችውና ለዚያ ክብር ያበቃቸው ሕዝብ በትዕቢታቸው ሊያወርዳቸውና አወዳደቃቸውንም ሊያከፋው እንደሚችል አለመረዳታቸው ነው።

ለነገሩ፤ “ሰው ሲ.ታጣ ፤ ይመለመላል ጎባጣ” እንዲሉ የዓለም የፖለቲካ ሁኔታ እየተለዋወጠ በሄደ ቁጥር፤ ምራዕባውያን በምሥራቅ አፍሪካ ላላቸው ጥቅም አይመቹም ያሏቸውን፤ አገራቸውንና ሕዝባቸውን አፍቃሪ የሆኑትን ድርጅቶች የቻሉትን ያክል ተረባርበው ካዳከሙ በኋላ፤ እንደ አማራጪ ሊቀርቡ የሚችሉ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች በሌሉበት ወቅት ተገኝተው እንጅ፤ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ከመጀመሪያ ጀምሮ በታሪካቸው ፖለቲካውን የጎርጥ እያዩ ኑሮቸውን በድሎት የገፉና፤ አንድ ትውልድ ለውጥ ፈልጎ እንደ ጉድ ሲጨፈጨፍ ድምጻቸውን አትፈተው ሃብታቸውን ሲያካብቱ የኖሩ ሰው እንጅ፤ በቅርብ ጊዜ በዲያስፖራው በዩ ፓል ቶኩ እንደተደለቀላቸው የሚያገሳ አምበሳ ሆነውም አያውቁም።

አስገራሚው ነገር ግን! እንዴት ነው ይህን ያክል ጊዜ እኛም ልንሸወድ፤ እሳቸውም ጉድጓዳችው በተዘጋጀበት የመጨረሻው የህይወት ጉዞአቸው ይህን ያክል ክህደት ለመፈጸም የወሰኑት? በጽናት መሞት ሲ.ገባ በክህደት? የወያኔ ቤተ ክህደት ለወዲያኛው ዓለም ኑሮ የተመቻቸ ይሆናል አሉ እንዴ? ዬእሳቸውን አካሄድ የሞኝ ጀሮ ያላቸው ተቀዋሚ ድርጅቶች እንዳይሰሙ ፍሩልኝ ወገኖች።

እኔም እንደ ሌሎቹ ወገኖቸ የፖለቲካ ምርጫው ጠባብ ሆኖብኝ፤ አምበሳ! አምበሳ ሲ.ሏቸው፤ የተቀዋሚ ተቀዋሚ እንዳልባል ውስጤ እያረረ፤ ይሁን እስኪ! አልኩ እንጂ፤ ቀደም ሲ.ል ጅምሮ ለህብረት በተደርጉት የፓሪስና የዋሽንግተን ጉባዔ ያደረጉት የትቢ.ት እምቢ.ተኝነት። በኋላም በምርጫ 97 ቅድመ ዝግጅት ወቅት ለቅድመ ምርጫ ማሟያ የቀረቡትን የህብረቱ የመደራደሪያ ነጥቦች ረግጠው፤ በትዕቢ.ት ህብረቱ ምንም ዓይነት አቅም እንዴሌለውና “አገሪቱን እንደ ቀትር እሳት በፖለቲካ ያቀጣጠልኩት እኔ ነኝ” በሚል ግትር አቋም ወደ ምርጫ ሲ.ገሰግሱ ነበር፤ ሌሎቹ እንደኔ እርማቸውን እስኪ.ያወጡ እንደ ዜጋ በትግሥት የጠበኩት።

አሁንም ምርጫ እስኪ.መጣ ሲ.ያደቡና፤ የምርጫ 97 የነፃና ዲሞክራሲ.ያዊ መስፈርት የሆኑትን ስምንት ጥያቄዎች ሳይሟሉ፤ የምርጫ ቸዋታ ውስጥ እንደማይገቡ ሲ.ምሉ ሲ.ገዘቱ ቆይተው በጠራራ ፀሐይ ሺ.ል አሉን። የሚገርመው ደግሞ ትንሽ እንኳ መልኩን ሳይቀይር እንደ ምርጫ 97ቱ፤ መድርኩ ይሟሉ ያላቸውን የነፃና ዲሞክራሲ.ያዊ ምርጫ መስፈርቶች ወደጎን አንከባለው፤ በዚ.ያን ሰዓት ህብረቱን በአቅሙ እንዳጣጣሉት አሁንም መድረኩን ከስም በስተቀር ምንም አይነት አቅም የሌለው ውዳሴ ከንቱ መሆኑን በድጋሚ አጣጥለው ማሰናበታቸው ነው። ( ለማስረጃ፤ በጥቅምት 2/2009 ዓ.ም በቅንጅት ሲ.ዊዘርላንድ የፖል ቶክ ክፍል የሰጡትን ቃለ ምልልስ ያዳምጡ)። በተለይ በዚ.ህ ቀን የትግሉን ጎራ መሰናበታቸውን የሚያሳዩ በአንደበታቸው ሲ.ነገሩ ለማድመጥ እድሉ ገጥሞኛል። በጣም ካስገረመኝ አንዱ ጥያቄና መልሳቸው “ክቡር እንጂነር ኃይሉ ሻወል፤ ይህ በሰሞኑ ሦስቱ ድርጅቶች የተፈራረማችሁት ውል በህገ-መንግሥቱ ውስጥ ተካቶ ለወደፊት እንደ ህግ እንደሚያገለግል ተጽፏል። ሌሎች በዚ.ህ ድርድር ያልተካፈሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ይህን ህግ ባይቀበሉትና ሊ.ደራደሩ ቢ.ፈልጉ እንዴት ያዩታል”? ኢንጅነር ሲ.መልሱ፤ “ይህን ህግ ፈጽሞ ዳግም ለድርድር ማቅርብ አይቻልም። ወደ ምርጫ የሚመጣ የተቀዋሚ ድርጅት ሁሉ ይህን ህግ የመቀበል ግዴታ አለበት” ። ኧረ የቆራጥ ህዝብ ያለህ!! ወያኔም እኮ፤ “እኔ ከማወጣው ህግ በስተቀር ስለ ህግ ለውጥና

መሻሻል መጠየቅ የማይታሰብ ነው” ሲለን ነው የቆየው። ኢንጂነሩ ከምኔው የወያኔ የታችኛው መንጋጋ ሊሆኑ ፈጠኑ?

ሌላው መብገኛ ደግሞ፤ የሳቸው ምክትል ተብሎ እዚሁ ስሜን አሜሪካ ከመጣ ዓመት በላይ ያስቆጠረው አቶ አባይነህ ብርሃኑ ባለፈው ዕሁድ በ11/01/09 ዓ.ም በኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ድምጽ የመወያያ ክፍል (VEDR) ቀርቦ፤ በውሉ ላይ ረቆ በአንቀጽ ያልተቀመጠ እንደ ሃቅ አድጎ ሊሞላን በዳዳው ስለ እስረኞች መፈታት፤ እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት ለሚቋቋመው የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚሽን ታስሩብኝ የሚላቸውን የፖለቲካ እስረኞችና የታሰሩበትን እስር ቤት አስመዝግቦ እንዲፈቱ ያደርጋል ብሎ ድብን አደረገን። ይህም በሁልት እጅ እራስ አስይዞ እግዚኦ ተሳህለን! የሚያሰኝ ነው።

አንድ የፖለቲካ ድርጅት አደረጃጀቱም ሆነ ጥብቅናው ለአገርና ለህዝብ ካልሆነ፤ የድርጅት መፍለቂያ የሆነውን የህ/ሰብ ድጋፍ እንዴት ነው የሚያገኘው? የፖለቲካ እስረኛ ማለት ከኢህአዴግ ጋር ግንኙነት ባለው የፖለቲካ ድርጅት ብቻ የሚለካ ማለት ነው? አገር ውስጥ ድርጅታቸው በህጋዊ መንገድ ስለማይንቀሳቀሱ እስረኞች ጥብቅና መቆም ለነሱ ውርደት ይሆን? እንደ ፀጋየ ገ/መድን፤ አበራሽ በርታ፤ ስጦታው ሁሴንና የመሳሰሉት የኢህአፓ አባላት ውሃ እንደበላቸው ይቅሩ ማለታቸው ነው። ከህዝብ አብራክ ከወጣው እውነተኛ የመኢአድ ምክትል ሊቀመንበር የሰማነው መርዶ ይህን ይመስላል።

ውድ ወገኖቸ! በአጠቃላይ በኔ እምነት፤ በተሰበረ ብርጭቆ ትኩስ ሻሂ ወይም ቡና መጠጣት ለካንሰር ነው። ተወደደም ተጠላም አባላቶቹ ካላዳኑት በስተቀር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል፤ መኢአድን አሳምረው ለወያኔ ሸጠውታል። ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የህብረት ጥንሥሶችን ሲረግጡና ለብቻቸው ሲጋልቡ የኖሩበት ሚስጥር አሁን ቁልጭ ብሎ በትግሉ ጎራ ላሉ ወገኖች ተረጋግጧል።

እሄን ያክል ስሜቴን ከግለጽኩ በኋላ፤ ታድያ አሁን ምን ይደረግ ነው የምትለን? የምትሉኝ ጥቂት እንዳልሆናችሁ እገምታለሁ።

***ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል በመኢአድ ስም ኢትዮጵያን ሌላ የአምስት ዓመት መከራ ሊጭኑባት አይገባም። የአመራር ምንጭ አባላት እንደሆኑ ሁሉ፤ ሁሉም የመኢአድ አባላት ሰሞኑን በየፖል ቶኩ እየሰሩ እንዳሉት የኢህ አዴግ ካድሬዎችን የመሰለ ድርቅና አቁመው፤ ከሌሎች ሃቀኛና ስር ነቀል ለውጥ ከሚሹ ወገኖቻቸው ጎን መሰለፍ ይጠበቅባቸዋል።

*** በአሁኑ ሰዓት በምርጫ 97 ህብርቱ እንዲሟሉ ይዞ የነበረውንና ኢንጅነር በቅንጅት ስም ያከሸፉትን አቋም ይዞ እየገፋ ያለውን መድረክ፤ በአቋሙ እንዲገፋና፤ ኢንጂነሩ ያበላሹትን እውነተኛ ታሪክ እንዲሰራ ከውጭም ከውስጥም ሁሉም ኃቀኛ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ድጋፉን ሊሰጥና ዬእምነት ጫና ሊያደርግ ይገባል።

*** አገር ውስጥ በህጋዊ መንገድ የማይንቀሳቀሱ ድርጅቶች በከፍተኛ ፍጥነት ችግሮቻቸውን ወደ ጎን ትተው አንድ ላይ በመቆም አደገኛ የሆነውን የኢንጅነር ኃይሉን

አካሄድ ጊዜ ወስዶ ሊቋጪ ከማይቻል ከፍተኛ ችግር ውስጥ አገራችንን ሳይጨምራት ማክሸፍ ይጠበቅባቸዋል።

*** በዓለም ዙሪያ ያለን እውነተኛ ኢትዮጵያውያን፣ የኢንጅነሩን አደገኛ አክሄድና፣ የዚህ ሥውር ደባ አጃቢ የሆኑትን የውጪ ኃይሎች አካሄድ ትክክል እንዳልሆነ በተቃውሞ ሰልፍ መግለጽ ይጠበቅብናል።

*** ከወያኔ/ኢህአዴግ ቁጥጥር ውጪ ያሉ እውነተኛ አገርና ሕዝብ አፍቃሪ የሆኑ መገናኛ ብዙኃን፣ በከፍተኛ ደረጃ የኢንጅነሩ ድርድር፣ የኢትዮጵያን ጥቅምና ለውነተኛ ለውጥ ያልታሰበ፣ ከሥልጣን ጥምና ጥቅም ጋር የተቆራኘ መሆኑን አጥብቀው ሊይስረዱ ይግባል።

*** በትጥቅ ትግል ሜዳ ላይ አለን የሚሉን ተቀዋሚዎች፣ ከወረቀትና ከተለያየ የሳይበር በረከተ ህይወት ወጥተው ምርጫ የሚባለውን የኢሃዴግ የልመና መሳሪያ ለማክሸፍና፣ ለጋሾቹም የኢትዮጵያን ህዝብ የመሰረታዊ ለውጥ ፍላጎት እነሱ እንደሚያስቡትና ከጥቅማቸው ጋር በሚያሰሉት ሽርፍራፊ ለውጥ እንደማይገዛ እንዲገነዘቡና፣ ኢህአዴግን ከጀርባቸው አውርደው፣ ለጥቅማቸው ሲሉ ከኛ ጋር እንዲሰለፉ ማስገደድ መቻል ያለበት ወቅት አሁን መሆኑን እንዲረዱ የማደርግ ኃላፊነት አለባቸው።

በአጠቃላይ በኔ ግምትና እምነት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ መሪ ድርጅት ያጣው ህይወታቸው፣ ህዝባቸውና አገራቸው መሆኑን አምነው በሙሉ ሰዓት ይታገሉና ይዋደቁ የነበሩ፣ ህዝባቸውን የመሰረታዊ ለውጥ ባለቤት ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ፍላጎት ያልነበራቸው የኢህአፓ አመራር አባላት በወያኔ እጅ ከወደቁ በኃላ፣ ቀሪዎቹ በወያኔ ሰርጎ ገብነትም ይሁን "ካረጁ አይበጁ እንዲሉ" በውስጣቸው የስልጣን ሽኩቻ ከተጠመዱና ከሁለት ከተከፈሉ ወዲህ፣ የተለጣፊዎች ገብያ እጅግ እንዲደራ አድርጎታል። በዚህ ጉዳይ አባላቶቹ እጅግ ሊቆጩ ይገባል። አሁንም በሚገባ አገራቸው ያለችበትን ውስብስብ የፖለቲካ ሁኔታ አጢነው፣ እንደልማዳቸው በጥዋት የገቡትን ቃል ኪዳን አድሰው፣ በአንድ ላይ ቆመውና በአሁኑ ሰዓት ትግሉን በሙሉ ሰዓት በ (Full time) ከያዙት ድርጅቶች ጋር ተባብረው የኢትዮጵያን ህዝብ ከወያኔ እና ትግሉን ከራሳቸው ጥቅም ጋር ከሚያሰሉ ተለጣፊ ድርጅቶች እጅ መታደግ ይኖርባቸዋል።

ኢትዮጵያ በሃቀኛ ልጆቿ ከውጭና ከውስጥ ጠላቶቿ፣
ተጠብቃ ትኖራለች!!!!!!!!